ሞዓ አንበሳ

Moa Anbesa

ከሞዓ አንበሳ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት

የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ

ታኅሣሥ ፲፩ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም.

ሞዓ አንበሳ እና የዘውድ ምክር ቤት እሑድ ታኅሣሥ ፲፩ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. ከቀኑ ስምንት ሰዓት እስከ አስራ ሁለት ሰዓት፣ በሊቀ መንበሩ በክቡር ዶክተር ጌታቸው መካሻ ሰብሳቢነት፣ የውይይት ስብሰባ ተካሄዷል። ሊቀ መንበር ዶክተር ጌታቸው መካሻ ሞዓ አንበሳ ከየት ወደየት፤ የአስራ ሦስት ዓመት ጉዞና ውጣ ውረድ፣ በሚል አርእስት ስለ ድርጅቱ እርምጃ ሰፋ ያለ መግለጫ ከሰጡ በኋላ፣ የውይይቱ መድረክ ለአባላት ክፍት ሁኖ ብዙ የሃስብ መለዋወጥ ተደርጓል።

ስብሰባው የተካሄደው ሥርዓትን የተከተለ፣ ሙሉ ኢትዮጵያዊ ጨዋነትና መከባበር በታየበት ውይይት ነበር። አቶ አበበ ተስፋ የሞዓ አንበሳ ጠቅላይ ጸሐፊ፤ አቶ ሥዩም አበራ የዘውድ ምክር ቤት ጸሐፊ፣ የድርጅቱን እንቅስቃሴና ሥራቸውን በተመለከተ፣ በተለይም በዋሽንግንተን ዲሲ አካባቢ ድርጅቱን ለማዳከም ስለተከናወነውና ስለሚካሄደው ሽኩቻ ሰፋ ያለ ገለጣ አድርገዋል ።

ይህንንም አስመልክቶ አስቀድሞ የተሰጠውን ሰፊ መግለጫ፣ በዋሽንግተን ዲሲ አካባቢ የሚገኙ ታላላቅ አንጋፋ ሬድዮ ማሰራጫዎች፣ ማለትም አንድ ኢትዮጵያ፤ ነፃነት ለኢትዮጵያ እና ሕብረት ሬድዮ ጣቢያዎች ለሕብረተሰቡ በማስደመጣቸው፣ የሞዓ አንበሳ እና የዘውድ ምክር ቤቱ የተነሳሱበትን የተቀደሰ ዓላማ ለሕዝብ ግልጽ በመሆኑ፣ አቅጣጫውን ለውጠው ለግል ጥቅም ለማዋልና ለማራከስ፣ በአንዳንድ ግለሰቦች ሲካሄድ የነበረውንና የሚካሄደውን ዘመቻ ለማክሸፍ ዛሬ የተወሰደው ቁርጠኛ እርምጃ ምን ያህል አስፈላጊ መሆኑን አረጋግጠናል።

ከስብሰባውም መጨረሻ የተሠጠው ውሳኔ የሚከተለው ነው፤

፩ ዘውድ የሕዝብ እንጂ የግለሰብ ወይም የአንድ ቤተሰብ የግል ንብረት አለመሆኑ በማረጋገጥ፤

፪ ዘውድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዓርማ፣ ታሪካዊ ቅርስ እና አኩሪ ጌጥ በመሆኑ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች አሰባሳቢ ሆኖ የሚሰለፍ መሆኑን ግልጽ በማድረግ፣

፫ ሞዓ አንበሳ ዛሬ በዘውድ ደጋፊነት የሚከራከር ሆኖ፣ ወደ ፖለቲካ ፓርቲነት ተለውጦ፣ ከሌሎች ፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር የሚወዳደር ኃይል መሆኑ፣

፬ አሁን በሞዓ አንበሳና በዘውድ ምክር ቤት ስም የሚነገዱ፣ ግዚያዊውን የኢትዮጵያ አስተዳደር የሚለማመጡ፣ ባሁኑ ግዜ የአገራችን ሕዝብ ባለበት የጭንቀት፤ የስደት ዘመን በመዘንጋት የሕዝብን አንድነት፤ ክብር፤ ሉአላዊነትና ሰቆቃ ለጊዜያዊ ምኞት መለወጥ በኢትዮጵያዊ ባሕልና ታሪክ እንዲሁም በእግዚአብሔር ፊት የሚያስጠይቅ መሆኑ ተስማምቷል።

፭ ሆኖም ዋሽንግተን ውስጥ ተሸሽገው በራድዮ ከመሳደብ በቀር ስማቸውን እንኳን ለመግለፅ የማይፈልጉ ውስጠገብ ሰዎች፣ ስህተታቸውን በመቀጠል፣ እንታረምም በማለት በአመፃቸው ጠንቅ ዘውዱን በሚጎዳ ክፉ ተግባራቸው ቢቀጥሉ፣ ተግባራቸው በሕዝብ ዘንድ ተጠያቂ እንደሚያደርጋቸውና ሕግና ሥርዓትን በማፍረሳቸው፣ ተገቢው ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ተወስኗል።

ኢትዮጵያ ታበጽህ እደዊሃ ሐበ እግዚአብሔር

ዶክተር ጌታቸው መካሻ

የሞዓ አንበሳ ሊቀ መንበር